የሰ/መ/ቁ. 20869

ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ከማል በድሪ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ጌታቸው ምህረቴ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡-** አቶ ፋንታሁን አባተ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ - ቀረቡ (ነ/ፈጅ እስክንድር)

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነውን ውሣኔ የሰጠው የፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በስራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ የተከፈለው የሁለት ወራት ቦነስ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የቦነስ ክፍያ ዋና አላማው ሠራተኛ በስራ ላይ በነበረበት ወቅት የሠራው ስራ ለአሠሪው ጥሩ ውጤት አስገኝቶ ከሆነ በስራ ላይ ያለው ሠራተኛ ለወደፊት ውጤታማ እንዲሆን ለማበረታታት እንጂ ስራውን የለቀቀ ሠራተኛ እንደመብት የሚጠይቀው አይደለም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም የቀረበውን ይግባኝ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች በስራ ላይ ለነበሩበት ጊዜ የተከፈለውን የቦነስ ክፍያ ለአመልካቹ ስራ በመልቀቃቸው ሊከፈላቸው አይገባም የተባለበትን ህጋዊ ምክንያት በመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ተጠሪ ተጠርቶ ቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው አመልካች ስራ ላይ በነበሩበት ወራት ለተሰራ ስራ የተከፈለው ቦነስ አመልካች ከሥራ ከተሰናበቱ በኋላ ሊከፈላቸው የሚገባ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች የተጠሪ መ/ቤት ሠራተኛ የነበሩና በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን ከለቀቁ በኋላ አመልካቹ በሥራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ለተሰራ ሥራ የቦነስ ክፍያ ለተጠሪ መ/ቤት ሠራተኞቹ መክፈሉ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ ፍ/ቤቶቹ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ያደረጉት የአመልካች የሥራ ውል በተቋረጠበት ጊዜ የተፈቀደ የቦነስ መብት ካለመኖሩም በላይ የቦነስ አላማው ሠራተኛው በሥራ ላይ በነበረበት ወቅት የሠራው ሥራ ለአሠሪው ጥሩ ውጤት አስገኝቶ ከሆነ ለወደፊትም

በተመሳሳይ መልኩ በርትቶ ውጤታማ እንዲሆን ለማበረታታት እንጂ ስራውን የለቀቀ ሠራተኛ እንደመብት የሚጠይቀው አይደለም በማለት ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን እንደተመለከትነው ቦነስ የሚከፈለው በስራ ላይ ያለ ሰራተኛ ወደፊት በርትቶ እንዲሰራ ለማበረታታት ብቻ ሳይሆን ሠራተኛው በስራ ላይ በነበረበት ወቅት የሰራው ሥራ ለአሠሪው ትርፋማ ውጤት በማስገኘቱ የትርፉ ተጠቃሚ እንዲሆንም ጭምር የሚሰጥ የጥቅም ክፍያ ነው፡፡ በመሆኑም የቦነስ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ለቦነስ ክፍያ ምክንያት ለሆነው ትርፍ ሠራተኛው አስተዋጽኦ ማድረግ አለማድረጉ ሊታይ ይገባል፡፡ በእርግጥ የሠራተኛው ሥራ ትርፋማ መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው የበጀት አመቱ ሂሳብ ከተሠራ በኋላ በመሆኑ የቦነስ መብት የሚፈቀደው ይኸው ውጤት ከታወቀ በኋላ ነው፡፡ የሂሳቡ ውጤት የአሠሪውን ትርፋማነት ካረጋገጠ ግን ለትርፋማነቱ አስተዋጽኦ ያደረገው ሠራተኛ የቦነስ ጥቅም ተካፋይ ሊሆን ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቹ በስራ ላይ በነበሩበት ጊዜ የተሰራው ሥራ ለመ/ቤቱ ትርፋማነት ምክንያት ሆኗል፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን የቦነሰ መብት የተፈቀደው አመልካቹ ከሥራ ከለቀቁ በኋላ ቢሆንም የቦነስ መብቱ የተፈቀደው የአመልካች በስራ ላይ በነበሩበት ወቅት ለተሠራ ሥራ በመሆኑ አመልካች የጥቅሙ ተካፋይ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ቦነስ በስራ ላይ ያለን ሠራተኛ ለማበረታታት ብቻ የሚሰጥ ነው በማለት የአመልካች የቦነስ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ሥህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16632 በ29/6/97 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37603 በ25/09/97 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በስራ ላይ ለነበሩበት ከሰኔ 24 ቀን 1995 እስከ ሰኔ 23/1996 ላለው ጊዜ ለሌሎች ሠራተኞች የተሰጠው ቦነስ እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# ኀብረት